# የኢትዮጵያ ታላቁ ሕዳሴ ግድብ 3ኛ ዓመት

# በሮም ተከበረ

የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የተጀመረበት 3ኛ ዓመት በዓል በሮም በሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት ግንቦት 3 ቀን 2006 ዓ.ም. በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ተከብሯል።

በእለቱ ክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ ለበአሉ ታዳሚዎች ባደረጉት ንግግር የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መሠረት የተጣለበትን 3ኛ ዓመት ዛሬ በጋራ ሲከበር የግንባታው ሂደት የደረሰበት ደረጃ ለቀጣይ ልማታችን የሚሰጠው



ጥቅም፣ ለአካባቢ አገሮች ልማትና ትስስር የሚያደርገው አስተዋጽኦና ሕዝባችንን ለአንድ አላማ በጋራ እንዲቆም ማስቻሉን በመዘርዘር ግንባታው ሌት ተቀን በመከናወን ላይ እንደሆነ፤ የቁሳቁስና የፋይናንስ አቅርቦትም በአስተማማኝ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ገልፀዋል።

በመቀጠልም በመንግሥትና በመላው የአገራችን ሕዝቦች የተጀመረውን ከድህነት የመላቀቅ ወሳኝ ትግል አንዱ የሆነውን የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ በማጠናቀቅ የጀመርነውን የልማት ጉዞ እውን ለማድረግ ቁልፍ ሚና የሚጫወተውን የሕዳሴ ግድብ ከፍጻሜው ለማድረስ የሚጠበቅብንን የገንዘብ፣ የእውቀትና የጉልበት ተሳትፎ ለማድረግ ቃላችንን ዳግም በማደስ እንደሆነ ገልፀው በሮም የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እስካሁን ላደረጉት ድጋፍ ምስጋና በማቅረብ ለወደፊቱም ድጋፋቸውን የበለጠ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።



በዚሁ ወቅት በሮም የተቋቋመው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ም/ቤት ያዘጋጀው የሕዳሴ ግድቡን ገጽታ የሚያሳይ ዶክመንተሪ ፊልም ለእይታ በማቅረብ፣ ሶስት የተለያየ መጠን ያላቸው ምስሎች በጨረታ የተሸጡ ሲሆን፤ የሕዳሴ ግድቡን በተመለከተ ሁለት ቀስቃሽ ግጥሞች በዲያስፖራ አባላት ቀርበዋል፡፡

በእለቱ ለታዳሚዎች ምግብና ቀላል መጠጦች በተመጣጣኝ ዋጋ የቀረቡ ሲሆን፤ አዝናኝ የሙዚቃ ዝግጅቶችም በባለሙያዎች ቀርበዋል፡፡



በመጨረሻም የእለቱ ታዳሚዎች «እንደ ጀመርነው እንጨርሰዋለን» የሚለውን መሪ ቃል በማደስ ከጨረታና ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎች 4,369 ዩሮ እና 31,000.00 ዩሮ ቦንድ ለመግዛት ቃል በመግባት (ከዚህ ውስጥ የሚሲዮኑ ሠራተኞች ቃል የገቡት ዩሮ 25,350.00) የእለቱ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

